# የሌበር አታሼ ተግባር፣ኃላፊነት እና አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የጋራ መመሪያ

**መመሪያ ቁ. 49/2013**

# የሌበር አታሼ ተግባር፣ኃላፊነት እና አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## መግቢያ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ የማድረግ እና የኢትዮጵያ ሚስዮኖችን የማስተባበር እንዲሁም የመቆጣጠር ሃላፊነት በውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 790/2005 አንቀጽ 3(4) እንዲሁምየፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1097/2011 አንቀጽ 13(10 እና 13)የተሰጠው በመሆኑ፤

በውጭ አገር የስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 አንቀጽ 14(1) የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር እና መንግስትን በማስፈቀድ ሌበር አታሼ በሰራተኛ ተቀባይ አገር በሚገኘው ሚሲዮን እንዲመደብ የማድረግ ሃላፊነት የተሰጠው በመሆኑ፤

ኢትዮጵያውያን በዉጭ አገር ለስራ በሚሰማሩባቸዉ አገራት በሚደረገው የሌበር አታሼ ምደባ እና አስተዳደር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ቅንጅት ግልጽ፣ወጥ እና ተቋማዊ በሆነ አሰራር ተግባራዊ የሚደረግበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

አዋጅ ቁጥር 923/2008 አንቀጽ 14 (2) የሌበር አታሼ ተግባርና ኃላፊነት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በጋራ በሚያወጡት የአሰራር መመሪያ እንደሚወሰን የደነገገ በመሆኑ

ይህ መመሪያ ወጥቷል፡-

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የሌበር አታሼ ተግባር፣ ኃላፊነትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 49 /2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ መሠረት

1. **"የሌበር አታሼ"** ማለት በኢትዮጵያ የውጭ አገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 አንቀጽ 14(1) መሰረት የስራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር እና መንግስትን በማስፈቀድ እንዲመደብ የሚደረግ ባለሙያ ነው፡፡
2. **"ሚሲዮን"** ማለት በዉጭ ግንኙነት አዋጅ ቁጥር 790/2005 አንቀጽ 2(4)በተደነገገው መሰረት የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ነው፡፡
3. **"የሥራ ስምሪት ኤጀንሲ"** ማለት በውጭ አገር ሥራ እና ሰራተኛን ለማገናኘት በኢትዮጵያ ወይም የሰራተኛ ተቀባይ አገር ፍቃድ የተሰጠው ኤጀንሲ ነው፡፡
4. **"የስራ ስምሪት"** ማለት በኢትዮጵያ የወጭ አገር የሥራ ስምሪት ሕግ መሰረት ወደውጭ አገራት የሚደረግ የሥራ ስምሪት ነው፡፡
5. **"የጋራ ኮሚቴ"** ማለት በኢትዮጵያ መንግስት እና በሰራተኛ ተቀባይ አገር መካከል በተፈረመው የስራ ስምሪት የሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት የተቋቋመ የሁለትዮሽ ኮሚቴ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## የሌበር አታሼ ምደባ፣ ተግባር እና ሃላፊነት

3. **የሌበር አታሼው ምደባ**

የሌበር አታሼው

1. ከዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር እና መንግስትን በማስፈቀድ በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኢትዮጵያዊያን ለስራ በሚሰማሩባቸው የመካከለኛው ምስራቅ አገራት እንዲመደብ ሊደረግ ይችላል፡፡

2. ማንኛዉም የሌበር አታሼ ከመመደቡ በፊት በዉጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 790/2005 አንቀጽ 34(1) እና አንቀጽ 24 መሰረት የተስማሚነት መመዘኛዎችን ማሟላቱ መረጋገጥ አለበት።

3. በሌበር አታሼነት የሚመደብ ባለሙያ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስፈላጊዉ ስልጠና ይሰጠዋል።

4. የሌበር አታሼው የሚሲዮን የሥራ ቆይታ ሶስት አመት ይሆናል።

5. **የሌበር አታሼው ተጠሪነት**

   1. የሌበር አታሼው በኢትዮጵያ የውጭ አገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 እና በዉጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 790/2005 አንቀጽ 34 በተደነገገው መሰረት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ስልጣን ስር የሚወድቁ ቴክኒካዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለዉ ግንኙነትና ተጠሪነት ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል።
   2. በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲመደብ የተደረገው ሌበር አታሼ የቅጥር ግንኙነት ከሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ነው።
   3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚሲዮን ቆይታዉ በሚያከናዉናቸዉ ተግባራት በዉጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 790/2005 አንቀጽ 34(2) መሰረት የሌበር አታሼው ተጠሪነት ለሚሲዮኑ መሪና ለዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል።

6. **የሌበር አታሼው ተግባር እና ሃላፊነት**

   1. የሌበር አታሼው ከሥራ ቅጥር ውሎች፣ ከአሰሪዎች እና ከኤጀንሲዎች ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ላይ ክትትል ያደርጋል።
   2. የሌበር አታሼው ከተመደበበት አገር የመንግስት አካላት ጋር ግንኙነት የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች በሙሉ ለሚሲዮን መሪው ያቀርባል፣ ጉዳዩን ይከታተላል፣ በሚሲዮን መሪው የሚሰጡ መመሪያዎችን ይፈጽማል።
   3. የሌበር አታሼው ከሚሲዮኑ መሪ እና ሌሎች ባልደረቦች ጋር በመተባበር የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናል፡

      ሀ. የሥራ ቅጥር ውሎች ሕግን ጠብቀው እንዲፈጸሙ ክትትል ያደርጋል፤

      ለ. ከሰራተኛ ውል አፈጻጸም እና አስተዳደር ጋር ተያይዞ የሚገጥሙ ችግሮች እንዲፈቱ ይሰራል፤

ሐ. ኢትዮጵያውያን ሰራተኞች ከአሰሪዎቻቸው፣ ከስራ ስምሪት ኤጀንሲዎች እንዲሁም በሥራ አጋጣሚ ከሚገናኟቸው ሌሎች ግለሰቦች እና ድርጅቶች ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች እንዲፈቱ ድጋፍ ይሰጣል፤

መ. የስራ ስምሪት ኤጀንሲዎች ከኢትዮጵያውያን ጋር ባላቸው ግንኙነት ሕግን ጠብቀው ስራቸውን እንዲያከናውኑ ክትትል ያደርጋል፤

ሠ. በተሰጠው ተግባር ስር ያሉ ሁነቶች እና ጉዳዮች ማስረጃ እና ማረጋገጫ እንዲቀርብባቸው ሲጠየቅ አግባብነት ባለው ሕግና አሰራር መሰረት አስፈላጊውን ስራ ያከናውናል፤

ረ. በሰራተኛ ተቀባይ አገር ያሉ የስራ ስምሪት ኤጀንሲዎች ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው ስለመሆኑ እና በቂ መጠለያ እንዳላቸው ያረጋግጣል፤

ሰ. የሥራ ስምሪት ትግበራው እንዲሻሻል እና የዜጎችን መብት ያስጠበቀ እንዲሆን አስፈላጊውን ተግባር ያከናውናል፤

ሸ. ሠራተኞች ስለመብታቸው፣ በስራ ውልና በአገሩ ሕግ መሠረት ያለባቸውን ግዴታዎች፣ በአገሩ መንግስት የሚሰጡ የነፃ ድጋፎች፣ ህገወጥ መሆን ስለሚያስከትለው ጉዳትና ሌላ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች በማሳተም ከአየር መንገድ ጀምሮ በሚያገኛቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ያሰራጫል ፤

ቀ. በሠራተኛና አሰሪ መካከል የሚፈጠር ልዩነት በመግባባት እንዲፈታ ምክር ይሰጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

በ. በተቀባይ አገር የሚፈለጉ የሠራተኞች ስልጠና ብቃት፣ የመብት ጥሰት፣ እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ መረጃ ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ውጤቱንም ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይልካል፤

ተ. የቅጥር ውል ጊዜያቸውን ጨርሰው ወደ አገር ሊመለሱ የሚፈልጉና ያልቻሉ ዜጎች የመመለስና የደመወዝ ክፍያ መብት መከበሩን ያረጋግጣል፤

ቸ. የሌቤር አታሼው ባለበት አገር መንግስት የሚወጡ የውጭ አገራት ዜጎች የሆኑ ሠራተኞችን የሚመለከቱ አዳዲስ ሕጎችና አሠራሮች፣ የአገሩ መንግስት ከሌሎች አገራት ጋር የተፈራረማቸውን ስምምነቶች እና ተያያዥ አሠራሮች በማጥናት ኢትዮጵያውያን ተመሳሳይ ወይም የተሻለ አያያዝ እንዲኖራቸው ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤

ኀ. የስራ ስምሪት የሁለትዮሽ ስምምነቱን አተገባበር፣ ስምምነቱ ያስገኘውን ጥቅም፣ የተስተዋሉ ጉድለቶችን እንዲሁም ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ወቅታዊ ግምገማ በማድረግ ለሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር *

Federal Democratic Republic ... Ministry of Foreign ...

ነ. በሁለትዮሽ የስራ ስምሪት የጋራ ኮሚቴ ስብሰባ እና ምክክሮች ወቅት ውይይት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ይለያል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

ኘ የሌቤር አታሼው ባለበት አገር ከሚገኙ የኢትዮጵያ ላኪ ኤጀንሲዎች ተወካዮች ጋር የጋራ የሆነ መደበኛ ግንኙነት እንዲኖር በማድረግ በሚያጋጥሙ የዜጎች መብት አከባበር ችግሮች ዙሪያ ያወያያል፣ ኤጀንሲዎቹ የሚጠይቁትን ድጋፍ ይሰጣቸዋል፤

አ. በሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሁም በሚሲዮኑ የሚሰጡትን ከስራው ጋር ተያያዥ የሆኑ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

7. የሌበር አታሼው እቅድ እና አፈጻጸም

በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲመደብ የተደረገ የሌበር አታሼ፡-

1. አመታዊ የሥራ ዕቅድ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ምክክር ይዘጋጃል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተዘጋጀውን እቅድ ከመፈጸም በተጨማሪ በሚሲዮን መሪው የሚሰጡትን ከሰራተኛ መብት አጠባበቅ ጋር የተያያዙ ተግባራት ያከናውናል፤
3. የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቱን ለሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ለሚሲዮኑ መሪ ያቀርባል፤
4. በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተመደበ የሌበር አታሼ የስራ አፈጻጸም ውጤት በሚሲዮን መሪዉ ተሞልቶ በየስድስት ወሩ ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይላካል፤

8. የሌበር አታሼው አስተዳደራዊ ደንቦች

1. የስራ ሰአት፣ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ፣ ሚሲዮኑ ከሚገኝበት ከተማ ውጪ የሚያደርጋቸዉ የግል ጉዞዎች፣ የግንኙነት ስርዓት፣ የንብረት አጠቃቀም፣ ስነምግባር እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን በተመለከተ የሌበር አታሼው ሌሎች የሚሲዮን ሰራተኞች በሚተዳደሩበት ሕግ እና ደንብ ይተዳደራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሌበር አታሼው የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተግባራዊ ለሚያደርጋቸው እና ለሚያወጣቸው አስተዳደራዊ እና የተጠያቂነት ሕጎች ተገዢ ይሆናል፡፡

9. የሌበር አታሼ የሥራ ቦታ እና አገልግሎቶች

1. የሌበር አታሼው የሥራ ቦታ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሚሲዮን ቅጥር ግቢ ውስጥ ይሆናል፡፡
2. ከዋና ሚሲዮን በተጨማሪ የሌበር አታሼዉ ኢትዮጵያውያን ሰራተኞች በብዛት በሚገኙባቸው እና የቆንስላ ወይም ሌላ ጽ/ቤት በተከፈተባቸው የተቀባይ አገር ግዛቶች ሊመደብ ይችላል፡፡
3. የሌበር አታሼው የሚሲዮኑን የድጋፍ ሰራተኞች እና አገልግሎቶችን ይጠቀማል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የጋራ እና የተናጠል ሃላፊነት እና የሥራ ቅንጅት

10.የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሃላፊነቶች

የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲመደብ ያደረገው የሌበር አታሼ

1. ለስራው አስፈላጊ የትምህርት ዝግጅት፣ አግባብነት ያለዉ የስራ ልምድ እና ክህሎት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
2. የሌበር አታሼው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12(3) በተደነገገው መሰረት ስልጠና እንዲሰጠው ያደርጋል፡፡
3. እንዲመደብ ላደረገው የሌበር አታሼ መደበኛ ደሞዝና ልዩ ልዩ አበሎች፣ ጥቅማ ጥቅሞች እና የሥራ ጉዞ ወጪዎችን ይሸፍናል፡፡
4. ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር የሌበር አታሼውን የአቅርቦት ወጪዎችን ይሸፍናል፡፡

11.የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሃላፊነቶች

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

1. ከሰራተኛ ተቀባይ አገር የመንግስት አካላት እና መንግስታዊ ተቋማት ጋር የሚደረጉ ማናቸውንም ግንኙነቶች ያከናውናል፤
2. የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሌበር አታሼ እንዲመደብ ባደረገበት አገር ኢትዮጵያውያን ሰራተኞችን የሚመለከቱ መደበኛ የቆንስላ ተግባራቱን ከሌበር አታሼው ተግባር እና ሃላፊነት ጋር የሚቀናጁበትን አሰራር ይዘረጋል፤
3. በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) መሰረት በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሸፈኑ ወጭዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለሌበር አታሼው የስራ ቦታ ያዘጋጃል አስፈላጊውን ግብአት ያሟላል፤
4. የሌበር አታሼውን ስራ ይከታተላል፣ አስፈላጊውንም ድጋፍ ይሰጣል፤

5. በሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለተመደቡ የሌበር አታሼዎች የሚከፈለዉን ደሞዝ፣ አበሎችና ሌሎች ወጪዎች እንዲሁም ለሥራ ማስኬጃ እንዲውል ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚላከውን ክፍያ ይፈፅማል፡፡

12.የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የጋራ ሃላፊነቶች

1. የሌበር አታሼ አመታዊ የሥራ እቅድ ያዘጋጃሉ፣ የሥራ እቅድ አፈጻጸሙን በጋራ ይገመግማሉ፤
2. የሌበር አታሼ ወጪዎች የሚተዳደሩበትን የተቀናጀ አሰራር በማዘጋጀት ይተገብራሉ፤
3. ለሌበር አታሼዎች የሚሰጠውን ስልጠና በጋራ በማዘጋጀት በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ተቋም አማካኝነት ይሰጣሉ፤
4. በዉጭ አገር የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ሰራተኞች ሁኔታዎች የሚሻሻሉበትን አሰራር በምክክር በማዘጋጀት ያስፈጽማሉ፤
5. አስፈላጊውን አስተዳደራዊ ቅንጅት በመተግበር ወጪ ቆጣቢ እና ውጤታማ አሰራር ይተገብራሉ፡፡

13.አስተዳደራዊ ቅንጅት

1. የሌበር አታሼው የአቅርቦት ግገር ሚሲዮኑ በዘረጋው ስርዓት መሰረት ይከናወናል፡፡
2. በዚህ መመሪያ የተደነገገው የስራ ክፍፍል እና የተጠሪነት ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት የሌበር አታሼው የሚሲዮኑ አባል ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
3. የሌበር አታሼውን የሚመለከቱ ማናቸውም የሰነድ ልውውጦች በሚሲዮኑ ስም እና መላላኪያ መንገድ ይተላለፋሉ

14.የተጨማሪ ሰራተኞች ቅጥር

1. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የኢትዮጵያውያን የስራ ስምሪት ክትትልንየሚያግዙ ሰራተኞችንበውስጥ መመሪያው መሰረት በጊዜ ገደብ ውል ሊቀጥር ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቀጠሩ ሰራተኞች የአገሩን ቋንቋ፣ ባህል እና የአኗኗር ዘይቤ የተገነዘቡ እና በተመደቡበት ቦታ ስራቸውን ለማከናወን እና ኢትዮጵያውያን ሰራተኞችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ለመፈጸም በቂ እውቀት እና ክህሎት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

15.መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ይህ መመሪያ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ስምምነት በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

16.መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሁለቱም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ከተፈረመበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ገዱ አንዳርጋቸው | ኤርጎጌ ተስፋዬ (ፒ.ኤች.ዲ)

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር | የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር

ሚያዚያ 29 ቀን 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ